# <u>ጾመ ሐዋርያት</u>

**ከዓቢይ ጾም ቀጥሎ ሁለተኛው ጾም የሐዋርያት ጾም ነው። የሰኔ ጾም
ይባላል። ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ ለስብከተ ወንጌ
ል ከመሔዳቸው በፊት የጾሙት ነው። ምእመናንም እነሱን ምሳሌ አ
ድርገው ከጰራቅሊጦስ በበነጋው ጀምረው ይጾሙታል። ይህ ጾም በሕ
ዝቡ ዘንድ የወታደር ጾም ይባላል። ለስብከተ ወንጌል «ዘመቻ» የተዘ
ጋጁት ሐዋርያት በጾሙት ተምሳሊት፤ በድሮ ዘመን ወታደሮች ለዘመ
ቻ ሲነሡ ወይም ከዘመቻ ሲመለሱ በተሳተ በተገደፈ ይቅር በለን ለማ
ለት በቀኖና ይጾሙት ነበር ማለት ነው። ይህ ጾም በመባጃ ሐመር ከ
ፍና ዝቅ ስለሚል የተወሰነ ቀን የለውም አንዳንድ ጊዜ ከአርባ ይበል
ጣል፤ አንዳንድ ጊዜ ከሠላሳም ያንሳል።**

**የዘንድሮ ጾመ ሐዋርያት ከግንቦት** 20 **እስከ ሐምሌ** 5
(Fast of the Apostles 28th May – 12th July)